# የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት
## ልሣነ- ሕግ ጋዜጣ

17ኛ ዓመት ቁጥር 81 አሶሳ
መስከረም 2001 ዓ.ም

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት
ም/ቤት ጠባቂነት የወ

**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ስለ ጥሬ ቆዳና ሌጦ ምርት የግብይት ሥርዓት ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 81/2001**

*መግብያ*

ክልላችን ከተያያዘው ፈጣን፣ ተከታታይና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገትን የማረጋገጥ ተልዕኮን በማሳካት ረገድ የቆጣና ሌጦ ምርት ወሳኝ ድርሻ የሚኖረው መሆኑን በመገንዘብ፣ የጥሬ ቆዳና ሌጦ አዘገጃጀትና ግብይት ሥርዓት በጥራት ደረጃ ላይ የተመሠረተ እንዲሆንና የምርት አሰባሰብ፣ አዘገጃጀት አከመቻቸትና አጓጓዝ ሂደት ተሻሽሎ ከንዑስ ዘርፍ ሊገኝ የሚገባው ጥቅም እንዲገኝ መደበኛ የግብይት ሥርዓትን መደንገግ በማስፈለጉ፣

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት የክልል ምክር ቤት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት የተሻሻው ህገ- መንግስት አንቀጽ 49/3/1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ምርት ግብይት ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 81/2001 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

1) "የግብይት ሥርዓት" ማለት ጥሬ ቆዳና ሌጦን የመሰብሰብ፣ የማዘጋጀት፣ የማጓጓዝና የመሸጥ ሂደት ነው፡፡

2) "ጥሬ ቆዳ" ማለት ከበሬ፣ ከወይፈን፣ ከላም፣ ከጊደር ወይም ከግመል የሚገኝ ትኩስ ወይም በአየር የደረቀ ወይም በጨው የተዘጋጀ ቆዳ ሲሆን ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ጥሬ ቆዳ ብሎ የሚሰይማቸውንም ያጠቃልላል፣

3) "ጥሬ ሌጦ" ማለት ከበግ፣ ከፍየል፣ ከጥጃ፣ ከአዞ ወይም ከዓሣ የሚገኝ ትኩስ ወይም በአየር የደረቀ ወይም በጨው የተዘጋጀ ሌጦ ሲሆን የክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ጥሬ ሌጦ ብሎ የሚሰይማቸውንም ያጠቃልላል፡፡

4) "ትኩስ ቆዳ ወይም ሌጦ" ማለት በጨው ያልታጀ ወይም በአየር ያልደረቀ እርጥብ ቆዳ ወይም ሌጦ ነው፡፡

5) "የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት" ማለት ጥሬ ቆዳና ሌጦን ለማሰባሰብ፣ ለማዘጋጀትና ለማጓጓዝ የሚያስችል ብቃት ያለው መሆኑን ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ነው፣

6) "የግብይት ተሳታፊዎች" ማለት በጥሬ ቆዳና ሌጦ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰብሳቢዎች፣አቅራቢዎች፣ ቄራዎችና ፋብሪካዎች ናቸው።

7) "ማጓጓዣ" ማለት ጥሬ ቆዳና ሌጦን ለማጓጓዝ አገልግሎት የሚሰጥ ተሽከርካሪ ሲሆን የጭነት እንስሳትንም ያጠቃልላል።

8) "አግባብ ያለው ባለስልጣን" ማለት የኤክስፓርት ግብይት ስርዓትን በሚመለከት ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ሲሆን የአገር ውስጥ ግብይት ሥርዓትን በሚመለከት የክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮና የቢሮ አካል የሆነ ዞን ወይም ወረዳ ማለት ነው።

9) "ቢሮ" ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ነው።

10) "ሴው" ማለት □ተ□ዓሮ ሰ□ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ተሣታፊዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

### 4. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

1) ማንኛውም ሰው የጥሬ ቆዳና ሌጦ ንግድ ፈቃድ ከማውጣቱ በፊት አግባብ ካለው ባለስልጣን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት ይኖርበታል።

2) የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘትም ሆነ ለማሣደስ መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሆኔታዎች በክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

### 5. ጥሬ ቆዳና ሌጦ ስለማዘጋጀትና ስለማጓጓዝ

1) ማንኛውም ቆዳና ሌጦ የሚያዘጋጀው ሰው ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የተሟላ የቆዳና ሌጦ ማደራጃ ድርጅት ሊኖረው ይገባል።

2) ጥሬ ቆዳና ሌጦ ከማደራጃ ድርጅት ወደ ሌላ አካባቢ መጓጓዝ የሚችለው ቢሮው በሚያወጣ መመሪያ መሠረት

ሲሆን ጭነቱ አግባብ ባለው አካል በሚመድብ ተቆጣጣሪ በኘሎምኘ መታሸግና በተቆጣጣሪው የተፈረመ የመሸኛ ወረቀት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

3) ማንኛውም ጥሬ ቆዳና ሌጦ የሚያጓጉዝ ሰው ለጭነቱ የሚሰጠውን የመሸኛ ወረቀት መያዝና አግባብ ባለው ባለስልጣን በተመደበ ተቆጣጣሪ ሲ□□ቅም ማሣየት አለበት፡፡

**6. የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት**

የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት በማንኛውም እርከን የኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃዎች ባለስልጣን በሚያወጣው የጥራት ደረጃ እና፣

1) ጥሬ ሌጦ ሲሆን በስፋት
2) ጥሬ ቆዳ ሲሆን በክብደት ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡

**7. ክልከላ**

1) ማንኛውም ሰው ንግድ ፈቃድ ሣይኖረው በጥሬ ቆዳና ሌጦ ንግድ መሰማራት አይችልም፣
2) ማንኛውም ሰው ጥሬ ቆዳና ሌጦ ወደ አልተፈቀደለት አካባቢ ማጓጓዝና መሸጥ አይችልም፡፡

**8. ስለ ግብይት መረጃ**

ማንኛውም የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ተሳታፊ የየራሱን፣

1) የየዕለቱን የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግዥ መጠንና ዋጋ፣
2) የየዕለቱን የጥሬ ቆዳና ሌጦ ሽያጭ መጠንና የተቀባይ ዝርዝር፣ እና
3) የየዕለቱን የገዛውን የጥሬ ቆዳና ሌጦ የጥራት ደረጃ መረጃ- ችን መዝግቦ መያዝና አግባብ ባለው ባለስልጣን ሲጠየቅ መስጠት አለበት፡፡

**9. ስለ ቁጥጥርና አስተዳደራዊ እርምጃዎች**

1) አግባብ ባለው አካል የተመደበ ተቆጣጣሪ መታወቂያውን በማሣየት የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና አዋጁ ን ለማስፈፀም የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን በአግባቡ መተግበራቸውን ይቆጣጠራል፡፡
2) የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ተሣታፊ ይህን አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ካላከበረ የንግድ ፈቃድ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፣
3) በክልሉ ልዩ ልዩ አዋጆች አግባብ ያለው ባለስልጣን የሚወስዳቸው አስተዳደራዊ

እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፈቃድ በሌለው ሰው ተከማችቶ ወይም ሲጓጓዝ የተገኘ የጥሬ ቆዳና ሌጦ እንደኮንትሮ-ባንድ ዕቃ ተቆጥሮ ተገቢው እርምጃ ይወሰዳል፣

4) ቆዳና ሌጦ ፈቃድ በሌለው ሰው መከማቸቱን ወይም መጓጓዙን ለጠቆመና ላስያዘ ሰው አግባብ ባለው ባለስልጣን ኮሚሽን እንዲከፈለው ይደረጋል ::

**10. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ሚያስፈልጉ ደንቦችን የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት፣ እና መመሪያዎችን ደግሞ የክልሉ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ሊያወጣ ይችላል።

**11. የተሸሩ ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ /በተመለከቱ/ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

**12. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በክልሉ የልሳኔ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከማውጣት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አሶሳ

ሐምለ 2001 ዓ/ም

አህመድ ናስር

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ

መንግስት ኘሬዝዳንት